መልእክት ሦስት

## ለሕይወታዊ አገልግሎቷ የቤተ ክርስቲያን ውስጠ-መሠረታዊ ግንባታ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኤፌ. 4፡11-16፤ ሮሜ. 12፡4-8፤ 1 ቆሮ. 12፡4-11፣ 28

1. **የቤተ ክርስቲያን ውስጠ-መሠረታዊ ግንባታ ፍጹማን በተደረጉ የክርስቶስ አካል ብልቶች ሁሉ በኩል ነው—ኤፌ. 4፡11-16፦**

   ሀ. የዐረገው ራስ ክርስቶስ በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ላሉ ቅዱሳን ፍጹም መደረግ ስጦታዎችን—ሐዋርያትን፣ ነቢያትን፣ ወንጌል ሰባኪዎችን እና እረኞችንና አስተማሪዎችን—ሰጥቷል—ቁ. 11-12፤ 1 ቆሮ. 12፡28፤ ሐዋ. 13፡1።

   ለ. የቅዱሳን ፍጹም መደረግ "ለአገልግሎቱ ሥራ፣ ለክርስቶስ አካል ግንባታ ነው"[1]—ኤፌ. 4፡12፦

      1. በኤፌሶን 4፡12 "ለ "የሚለው ቃል "ድምዳሜ"፣ "ለዚህ አላማ" ወይም ለዚህ ግብ" ማለት ነው።
      2. ስጦታው ያላቸው ብዙ ሰዎች አንድ አገልግሎት ብቻ አላቸው፣ ያም ለክርስቶስ አካል፣ ለቤተ ክርስቲያን ግንባታ ክርስቶስን ማገልገል ነው፤ ይህ በአዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ልዩና ብቸኛ የሆነው አገልግሎት ነው—2 ቆሮ. 4፡1፤ 1 ጢሞ. 1፡12።
      3. በ ኤፌሶን 4፡12 ሰዋሰዋዊ አወቃቀር መሠረት የክርስቶስ አካል ግንባታ የአገልግሎቱ ሥራ ነው፦

         ሀ. እንደ አገልግሎቱ ስራ ስጦታ ያላቸው ሰዎች የሚያደርጉት ነገር ሁሉ መሆን ያለበት ለክርስቶስ አካል ግንባታ ነው—ቁ. 12፣ 16።

         ለ. ይህ ግንባታ የሚከናወነው ስጦታ ባላቸው ሰዎች በቀጥታ ሳይሆን ስጦታ ባላቸው ሰዎች ፍጹማን በተደረጉ ቅዱሳን ነው፤ የስጦታዎቹ ሥራ በቀጥታ አይደለም፣ የቅዱሳን ሥራ ግን በቀጥታ ነው—ቁ. 11-12።

         ሐ. ስጦታዎቹ በመቀናጀት በአንድ ላይ የተጋጠሙት [ቅዱሳን] እያንዳንዳቸው የአገልግሎቱን ሥራ በመሥራት አገልግሎታቸው ይወጣ ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ያሉ ቅዱሳንን ፍጹማን ለማድረግ ነው—ቁ. 11-12።

         መ. በዚህ መንገድ፣ ስጦታ ባላቸው ፍጹም በመደረግ በኩል ቅዱሳን ሁሉ የአገልግሎቱን ሥራ ይሠራሉ፣ በመጨረሻም የክርስቶስ አካል ይገነባል—ቁ. 12፣ 16።

   ሐ. በመጨረሻም፣ የክርስቶስ አካል ብልቶች ሁሉ "የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፣ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን" ይደርሳሉ—ቁ. 13፦

      1. በቁጥር 3 ላይ ያለው የመንፈስ አንድነት በእውነታ ደረጃ የመለኮታዊ ሕይወት አንድነት ነው፣ በቁጥር 13 ላይ ያለው አንድነት ደግሞ ተግባራዊ በሆነ ደረጃ የኑሯችን አንድነት ነው፦

         ሀ. የእውነታ አንድነት ተግባራዊ ልምምድ ሊሆን እና በዚህም በተግባራዊ ደረጃ ያለ አንድነት ሊሆን ይገባል—ቁ. 3፣ 13።

         ለ. በቁጥር 13 ላይ *እስክንደርስ* የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተግባራዊ በሆነ ደረጃ የኑሯችን አንድነት ጋር እንደርስ ዘንድ ሂደት እንደሚያስፈልግ ነው፤ በእውነታ ደረጃ ያለው አንድነት ጅማሬው ነው እና በተግባራዊ ደረጃ ያለው አንድነት ደግሞ መድረሻው ነው።

      2. ተግባራዊ በሆነ ደረጃ ያለው አንድነት የእምነት አንድነት ነው—ቁ. 13፦

         ሀ. *እምነት* የሚያመለክተው የማመናችንን ድርጊት ሳይሆን የምናምንባቸውን ነገሮች፣ እንደ መለኮታዊው የክርስቶስ ማንነትን እና ለመዳናችን የተፈጸመው የቤዛነት ሥራውን ነው—1 ጢሞ. 1፡19፤ 6፡10፣ 12፣ 21፤ ይሁዳ 3።

         ለ. በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ልዩ የሆነ አንድ ነገር ብቻ አለን—እምነት፤ አማኞችን ለመቀበል ከእምነት በተጨማሪ ሌላ ነገርን የግድ ማለት ከፋፋይ መሆን ነው—ሮሜ 14፡1፤ 15፡7።

      3. ተግባራዊ በሆነ ደረጃ ያለው አንድነት የእግዚአብሔርን ልጅ በሙላት በማወቅ የሚገኝ አንድነት ነው—ኤፌ. 4፡13፦

         ሀ. የእግዚአብሔርን ልጅ በሙላት ማወቅ ለልምምዳችን የእግዚአብሔርን ልጅ እንደ ሕይወት በተመለከተ ያለውን መገለጥ መረዳት ነው—ማቴ. 16፡16።

---

[1] ከእንግሊዝኛው ሪከቨሪ ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ የተተረጎመ

ለ. የእምነት አንድነት በአጠቃላይ የሚመረኮዘው የእግዚአብሔርን ልጅ በሙላት በማወቅ ላይ ነው፤ ክርስቶስን እንደ ማዕከል ስንወስደውና እርሱ ላይ ስናተኩር ብቻ የእምነት አንድነት ላይ መድረስ እንችላለን፣ ምክንያቱም እምነታችን አንድ መሆን የሚችለው በእግዚአብሔር ልጅ ውስጥ ብቻ ነውና—ዮሐ. 20፡31፤ ገላ. 1፡15-16፤ 2፡20፤ 4፡4፣ 6፤ 1 ቆሮ. 2፡2።

4. "ሙሉ ሰው" ወደ መሆን መድረስ ወደ ሕይወት ብስለት መድረስ ነው፤ ተግባራዊ ለሆነ አንድነት ብስለት ያስፈልጋል—ኤፌ. 4፡13።

መ. ለክርስቶስ አካል ግንባታ "በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ" እናድግ ዘንድ እውነትን በፍቅር መያዝ ያስፈልገናል—ቁ. 15፡-

1. ወደ ክርስቶስ ማደግ ሙሉ ሰው ወደመሆን እስክንደርስ ድረስ በሁሉ ነገር ክርስቶስ በእኛ መጨመሩ ነው።

2. በኤፌሶን 4፡15 *ራስ* የሚለው የሚያመለክተው በክርስቶስ መጨመር የሆነው የሕይወት እድገታችን ራስ ከሆነው ሥር በአካሉ ውስጥ ያለ የብልቶች እድገት መሆን እንዳለበት ነው።

ሠ. በሕይወት ማደግ ራስ ወደሆነው ወደ ክርስቶስ ማደግ ሲሆን በአካሉ ውስጥ *መሥራት* ደግሞ ከእርሱ የተነሣ *መሥራት* ነው—ቁ. 15-16፡-

1. በመጀመሪያ ራስ ወደሆነው እናድጋለን፤ ከዚያም ለአካሉ ግንባታ ራስ ከሆነው ውስጥ የሚወጣ የሆነ ነገር ይኖረናል—ቁ. 16።

2. በሕይወት እድገትና በስጦታዎች መዳበር እያንዳንዱ የክርስቶስ አካል ብልት ለአካሉ እድገት የሚሠራ የራሱ ልክ አለው።

3. የክርስቶስ አካል እድገት የክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን መጨመር ነው ይህም በአካሉ በራሱ የአካሉን መገንባት ያመጣል—ቁ. 16።

## II. የቤተ ክርስቲያን ሕይወታዊ አገልግሎት በክርስቶስ ሕይወታዊ አካል እና በየአጥቢያው ባለ የክርስቶስ ሕይወታዊ አካል መገለጥ ውስጥ ነው—1 ቆሮ. 1፡2፤ 12፡27-28፤ ሮሜ. 12፡4-8፤ 1 ቆሮ. 12፡4-11፡-

ሀ. እኛ ይህ ሕይወታዊ አካል ስለሆንን፣ ሕይወታዊ መሆንና በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ሕይወታዊ በሆነ መንገድ ማገልገል ያስፈልገናል—ሮሜ 12፡4-5፡-

1. ለድሰታችን ሕይወታችን ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ጸጋ በክርስቶስ እንደ መለኮታዊው ንጥረ-ነገር ወደ ማንነታችን ውስጥ ሲመጣ፣ በክርስቶስ አካል ውስጥ ማገልገል እንችል ዘንድ ከሕይወት እድገታችንን ጋር አብሮ በሕይወት ወደሆነ ስጦታዎች የሚዳብሩ መንፈሳዊ ተሰጥኦዎችን እና ችሎታዎችን ከራሱ ጋር ይዞ ይመጣል—ቁ. 6-8።

2. አካሉ በሙሉ ሲሠራ፣ የአካሉን በፍቅር መገንባት በማምጣት አካሉ የራሱ እድገት ምክንያት ይሆናል—ኤፌ. 4፡16።

ለ. የክርስቶስ ሕይወታዊ አካል ሕይወታዊ አገልግሎት በአካሉ አጥቢያዊ መገለጥ ውስጥ እና በእግዚአብሔር አሠራር ውስጥ ባለ የሦስታንዱ አምላክ እንቅስቃሴ፣ በጌታ አገልግሎቶች በኩል እና ለክርስቶስ ሕይወታዊ አካል ብልቶች በመገለጡ በመንፈስ ስጦታዎች በኩል ነው—1 ቆሮ. 12፡4-11፣ 28፡-

1. በ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡4-6 የእግዚአብሔር አብ አሠራሮች፣ የእግዚአብሔር ወልድ አገልግሎቶችና የእግዚአብሔር መንፈስ ስጦታዎች አሉ።

2. የመንፈስ ስጦታዎች የጌታን አገልግሎቶች ለማከናወን ናቸው፣ የጌታ አገልግሎቶች ደግሞ የእግዚአብሔር አብን አሠራሮች ለመፈጸም ናቸው—ቁ. 4-6።

3. ሕይወታዊ በሆነ መንገድ ስናገለግል ሳለን በውስጣችን ያለው ሦስታንዱ አምላክ አብሮን ይንቀሳቀሳል።

4. ሦስታንዱ አምላክ ከእኛ ውጪ አይንቀሳቀስም፤ እኛ ስንንቀሳቀስ እርሱ ይንቀሳቀሳል—ኤፌ. 3፡16-17፤ 2 ቆሮ. 13፡14፤ 1 ቆሮ. 12፡4-6።

ሐ. የቤተ ክርስቲያን ሕይወታዊ አገልግሎት ለክርስቶስ ሕይወታዊ አካል፣ ሁሉን በሁሉ የሚሞላ ሁሉን-ያካተተው ሙላት ለሆነችው ለቤተ ክርስቲያን መገንባት ነው—ኤፌ. 1፡23።

*© 2021 Living Stream Ministry*